www.abyssinialaw.com




| 16ኛ ዓመት ቁጥር 12<br>16th year No. 12 | ባህር ዳር ህዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም<br>Bahir Dar 12th, Nov.2010 |
|---|---|


# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA


| የአንዱ ዋጋ ብር 12.76 Price Birr | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ. 312 P.O.Box |
|---|---|---|---|


| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| ደንብ ቁጥር 78/2003 ዓ/ም | Regulation No. 78/2010 |
| በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የዞን አስተዳደሮች እንደገና ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ ደንብ | The Revised Amhara National Regional State Zonal Administrative Reestablishment and Determination of Powers and Duties, Council of the Regional Government Regulation. |

| ደንብ ቁጥር 78/2003 ዓ/ም | Regulation No. 78/2010 |
|---|---|
| በአማራ ብሄራዊ ክልል የተሻሻለዉን የዞን አስተዳደሮችን እንደገና ለማቋቋምና ስልጣንና ተግባራቸዉን ለመወሰን የወጣ የክልል ማስተዳደር ምክር ቤት ደንብ | A REVISED REGULATION ISSUED BY THE COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT TO PROVIDE FOR THE RE-ESTABLISHMENT AND DETERMINATION OF POWERS AND DUTIES OF ZONAL ADMINISTRATIVES IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE |

www.abyssinialaw.com


የብሄራዊ ክልሉን የህዝብ ብዘት፣ የቆዳ ስፋትና ሚከአምድራዊ አቀማመጥ ግምት ወስጥ በማስገባት አስፈላጊነታቸው እየታየ በተመረጡ ስፍራዎች ክልላዊ ማተዳደሩን ወክለው ከወረዳዎች አቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮችን በተማከለ አግባብ የሚከታተሉ፣ የልማት ስራዎችን የሚቀናጁ፣ የሚያስተባብሩና የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ልማት ስራዎችን ለማፋጠንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን እንዲያግዙ ታስበው ለሚቋቋሙ ተቋማትና ለሚዘረጉ ፕሮግራሞች የተሟላ አፈጻጸም ሁለንተናዊ ድጋፍ የሚሰጡ የተዋረድ አስተዳደራዊ እርከኖችን ማደራጀት ተገቢ ሆኖ በማኘቱ፣

Whereas, it has been found out to be appropriate to set up hierarchical administrative structures that render an all-out support to complete performance of those institutions established and programs launched with the view to promote socio-economic developmental activities and to rule over good governance, follow up in central manner and handle matters beyond the capacity of the woredas, integrate and co-ordinate developmental activities, being designated as agents of the regional government in selected and identified areas of importance, taking in to account the territorial expanse of the National Regional State, destiny of its population, and geographical features;

በነዚህ አደረጃጀቶች አማካኝነት ለክልሉ ሕብረተሰብ ብቃት ያለውና የተመጣጠነ አስተዳዳራዊ አገልግሎት መስጠትና የተፋጠነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት የሚከናወንበትንና ሕ ቡ ዘላቂ ተጠቃሚ ት የሚረጋገጥበትን ምቹና የተረጋጋ ሁኔታ ፈጥሮ መንቀሳቀስ በማስፈለጉ፤

Whereas, it has, as a result of these organizations, become necessary to move forward by creating a conducive and stable condition whereby an efficient and balanced administrative service could be provided to the inhabitants on the regional state, rapid economic and social development accomplished and sustainable beneficiary of the population insured;

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳደር ም/ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገመንግሥት አንቀጽ 60 ንዑስ አንቀጽ 3/ሸ/ና አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ/7/ ድንጋጌዎች ሥር በተሠ ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

Now, therefore, the Council of the Regional Government of the Amhara National Regional State, pursuant to the power vested in it under the provision of Article 60 sub art. 3/H/ and Article 58 sub art. /7/ of the revised National Regional Constitution, hereby issues this regulation as follows.

www.abyssinialaw.com


# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የተሻሻለው የዞን አስተዳደሮች እንደገና ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ □ልል መስተዳደር ም/ቤት ደንብ ቁጥር 78/2003 □.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

1. "የዞን አስተዳደር" ማለት ለአስተዳደራዊ ምቹነትና ለሁለገብ የልማትም ሆነ የመልካም አስተዳደር ሥራዎች ሙሉ ተፈፃሚነት ሲባል የክልሉ ርዕስ መስተ□□ር ተ□ሪ □/ቤቶችን እንዲያቋቁምበት በዚህ ደንብ የተወሰነ ወይም የሚወሰንና በወስጡ የታቀፉ ወረዳዎች የሚካለሉበት አካባቢ ነው፣

2. "ጽ/ቤት" ማለት የዞን አስ/ጽ/ቤት ነው።

# PART ONE

# GENERAL

## 1. Short Title

This regulation may be cited as "The Revised Zonal Administrative Reestablishment and Determination of Powers and Duties Council of Regional Government Regulation No. 78/2010".

## 2. Definition

Unless the context requires otherwise, in this regulation:-

1. "Zonal Administrative" means an area describing those places selected to serve as centers of Woredas embraced therein, which is decided or to be decided in this regulation, whereby representative offices accountable to the Head of the Regional Government may be established for an administrative convenience and implementation of all embracing developmental as well as good governance activities.
2. "Office" means the zonal administrative office.

www.abyssinialaw.com


# ክፍል ሁለት

## ስለ ዞን አስተዳደሮች መቋቋምና ሥልጣን

### 3. ስለመቋቋምና ተጠሪነት

1. በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ ከዚህ በታች የተመለከቱት የዞን አስተዳደሮች ተቋቁመዋል፡-

   ሀ. የምዕራብ ጐጃም ዞን አስተዳደር
   ለ. ምሥራቅ ጐጃም ዞን አስተዳደ
   ሐ. የሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር
   መ. የደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር
   ሠ. የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር
   ረ. የደቡብ ጐንደር ዞን አስተዳደርና
   ሰ. የሰሜን ጐንደር ዞን አስተዳደር

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተመለከቱት የዞን አስተዳደሮች ሥራቸውን የሚያከናውኑት የክልሉን መስተዳድር በመወከል ሲሆን ተጠሪነታቸውም ለተጠቀሰው ምክር ቤትና ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል፡፡

3. የብሔረሰብ አስተዳደሮችን አደረጃጀትና ሥልጣን አስመልክቶ በተሻሻለው የክልሉ ሕገ መንግሥት ምዕራፍ ስምንት ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብነት ያላቸው የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ በሚገኙት የአዊ፣ የዋግ ኽምራና የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደሮች ላይም በተመሣሣይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

# PART TWO

## ESTABLISHMENT AND POWERS OF ZONAL ADMINISTRATIVES

### 3. Establishment and Accountability

1. The following zonal administrations are established in the regional state.

   **A.** West Gojjam Administrative Zone
   **B.** East Gojjam Administrative Zone
   **C.** North Shoa Administrative Zone
   **D.** South Wollo Administrative Zone
   **E.** North Wollo Administrative Zone
   **F.** South Gondar Administrative Zone
   **G.** North Gondar Administrative Zone

2. The Zonal Administratives, indicated under sub art. /1/ of this Article hereof, shall carry out their functions on behalf of the regional government and their accountability being to the council and head of the regional government.

3. Without prejudice to what has been provided for under Chapter 8 of the revised constitution as regards the organization and powers of the nationality administrations, the relevant provisions of this regulation shall mutatis mutandis apply to the Awi, Wag Hemera and Oromo nationality administrations with the National Regional State.

www.abyssinialaw.com


2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ሥር የሰፈረው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የዞን አስተዳደር ምክር ቤት በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ልዩ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የዞን የዋና ዋና ዓላማ አስፈላፃሚ መ/ቤቶችና እነርሱ የሚመሯቸው ሌሎች ተቋማት የሥራ እቅድና በጀት አፈፃፀም ግልጽነት ባለወና ወጤታማ በሆነ መንገድ ወቅቱን ጠበቆ የሚቀርብበትንና የሚገመገምበትን የሚከታተያና የሚገመግም ስልት ረቂቅ መርምሮ ያፀድቃል፣

ለ/ በከባቢው የሚገኙ ወረዳዎችን የልማትና የፋይናንስ እቅዶች በየምክርቤቶቻቸው አማካኝነት ተመክሮባቸው ከፀደቁ በኋላ ሲላኩለት አጠቃሎና ገምግሞ ለክልሉ ማስተዳድር ም/ቤት ያስተላልፋል ሲፈቀድም ተፈፃሚ ታቸወን ያቀላጥፋል፣

ሐ/ በዞኑ የሚሸፈኑ ወረዳዎችን ሥራ አፈፃፀም ብቃት ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይቀይሳል፣

መ/ በወረዳ መካከል የሚፈጠር አለመግባባት ቢኖር በሰላማዊ መንገድ የሚፈታበትን ብልሃት ያፈላልጋል፣ ከአንድ በላይ በሆኑ ወረዳዎች መካከል የቅንጅታዊ ተግባር አስፈላጊነት መኖሩ ሲታመንበት በዚሁ ላይ መክሮ በዋና አስተዳዳሪው በኩል ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ወገኖች እንዲተላለፍና ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

ሠ/ ከወረዳዎች በኩል የሽግሽግና የአደረጃጀት ጥያቄዎች ሲቀርቡ የመጨረሻ ውሣኔ የሚሰጠው አካል በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የክልሉ ማስተዳድር ም/ቤት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ

2. Without limiting the generality stated under sub article /1/ of this Article, the council of zonal administration shall, in accordance with this regulation, have the following powers and duties:-

a) examine and approve the draft of the corrective and remedial method used to evaluate, in a brief and effective way and on time, the plan and budget implementation of the main objective executors of the zonal offices and other organizations directed by them;

b) After receiving the developmental and financial plans, which are discussed and approved under their councils, of woredas found around, evaluate, conclude, and transfer same for the council of regional government;

c) Design a system that enables to develop the work efficiency of woredas covered in the zone;

d) Find a technique to resolve, if there is an occurrence of disagreement between woredas, it in a peaceful manner. When the necessity of task integration between more than one woredas is believed, by deliberating on the case, cause to be implemented and transferred it to the concerned proximate through the chief administrator;

e) Without prejudice to the Council of the Regional Government is being the last decision maker for queries of readjustment and organization raised

www.abyssinialaw.com



የመጀመሪያ ደረጃ ማጣራት እንዲካሄድ አድርጎ በጉዳዩ ላይ መሠረታዊ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣ ለተገቢው አካል አቅርቦ ያስወስናል፣

ረ/ በዋና አስተዳዳሪው ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት የዞኑ ነዋሪ ሕዝብ ሠላምና ደህንነት በአስተማማኝና በዘላቂነት የሚጠብቅበትንና የህግ የበላይነት የሚረጋገጥበትን ረቂቅ ስትራቴጅ መርምሮ ያፀድቃል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣

ሰ/ በዞኑ ወስጥ የሚገኘው የመንግስትና የሕዝብ ሃብትና ንብረት በተገቢው መንገድ ሟዘንና ከብክነት ማጠበቁን የሚያረጋግጥ ስርዓት ይቀይሣል በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

ሸ/ በዞን ወስጥ በሚገኙ፣ ሕጋዊ ባለቤት በሌላቸዉና ከአንድ በላይ የሆኑ ወረዳዎችን የተሟከለ ጥቅም በሚወክሉ ሃብቶችና ንብረቶች አያያዝና አስተዳደር ላይ መክሮ ውሣኔዎችን ያሣልፋል፣

ቀ/ በዞኑ የሚገኙ ከተሞችን ዘላቂና የተፋጠነ እድገት በሚያረጋግጡ አመቺ ሁኔታዎች ላይ መክሮ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትን ድጋፍ በሚፈላለግ የማዘጋጃ ቤት ሥራዎችን ያግዛል፣

በ/ የዞኑን ልዩ ትኩረት በሚሹ የንግድ፣ የኢንዱስትሪና በአጠቃላይም የኢንቨስትመንት አማራጮች ላይ በየጊዜው እየመከረ የማበረታቻና የማስተዋወቅ እርምጃዎች የሚወሰዱበትን ዘደዎች ያፈላልጋል፣

ተ/ የፌደራሉም ሆነ የክልሉ አስፈፃሚ አካላት ዝርዝርና

from woredas, pursuant to Article 58 Sub Article /2/ of the regional constitution, cause to be done the first instance investigation and put basic direction on the case, and submit same for the appropriate body to be determined;

f) Examine and approve the strategy draft, where it is prepared and submitted by the chief administrator, planned to keep the peace and security of the people living in the zone with reliable and sustainable way, and to ensure rule of law; follow-up it has been implemented;

g) Design a system that ensures the governmental and public wealth and property found in the zone managed in a proper manner and kept out from wastage, and cause same put into effect.

h) Provide a deliberated decision on the handling and management of wealth and properties found in the zone, which have not legal owner, and delegate the middling benefit of woredas more than one.

i) Help the duties of Municipality, deliberating on favorable situations that ensure sustainable and fast development of cities found in the zone, by searching for the support of governmental and non-governmental organizations.

j) Search for methods that yield reinforcing and introducing measures, on trade, industrial and in general alternatives of investments that need zonal emphasis.

k) Without prejudice to the detail and

www.abyssinialaw.com


የተናጠል ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ ወረዳ በላይ በሚገናኙ የመሠረተ ልማትና የአገልግሎት ማከፋ አወታሮች እቅድ፣ ግንባታ፣ ጥገና፣ ሥርጭትና አጠቃቀም ጉዳዮች ላይ ማክሮ መሠረታዊ አቋሞችን ይወስዳል፣

ቸ/ ለአስተዳደር ምክር ቤቱ አባላት ተጠሪነት ያላቸው የሴክተር መ/ቤቶች በየተሰጣቸው የሥራ ድርሻ እየተንቀሳቀሱ ለእናት ማሥሪያ ቤቶቻቸውና ተጠሪ ለሆኑለት አካል ወቅታዊ ሪፖርቶችን እንደሚቀርቡ ቢታመንም በተናጠል የሚከናወነው የእያንዳንዱ መንግስታዊ አካል ተግባር ዞን አቀፍ በሆነ መንገድ ተቀናጅቶና ተደጋግፎ የሚደበትንና ለህብረተሰቡ ጥራቱን የጠበቀ መንግስታዊ አገልግሎት ቀጣይነት ያለው ዋስትና የሚጥበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተፈፃሚነቱን ያረጋግጣል፣

ኃ/ በዋና አስተዳዳሪው በኩል በየጊዜው ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የዞኑን የተጠቃለለ ሪፖርት መርምሮ ያፀድቃል፣

ነ/ በዋና አስተዳዳሪው ወይም እንደተገቢነቱ በሌሎች የም/ቤቱ አባላት በሚቀርለትና በዚህ ንዐስ አንቀጽ ባልተሸፈኑ ሌሎች አስፈላጊ አጀንዳዎች ላይ ተነናግሮ ይወስናል።

**3.** የዞን አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በዚህ ደንብ በተሰጣቸው የወል ሥልጣናቸው መሠረት መክረው ለሚጼድሙት ማቸወም ተግባርና ለሚያሳልፉት ውሣኔ የጋራ ኃላነትና ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል።

individual responsibility of the federal and regional executive bodies, discusses and takes a fundamental stands on the plan, construction, maintenance, distribution, and usage of infrastructures and servicing cords that adjoins woredas more than one.

l) Even if it is believed that sectorial offices that are accountable to the council of the administration, moving through their work share given, shall submit periodic reports to their own office or to the body, that they are accounted. Device a mechanism by which qualified governmental service and annexing guarantee for the community being undertaken, and individual task performance of each governmental organ be operated with zonal integration and collaboration way. Confirm its implementation.

m) Examine and approve the summarized zonal report that is prepared and submitted by the chief administrator.

n) Discuss and decide on agendas submitted by the chief administrator or as its importance by other members of the council, and other essential agendas not covered in this sub article.

3. Members of the council of zonal administration shall have a collective responsibility and accountability for their any execution of deputy and decision rendered deliberately, in accordance with the common powers vested by this regulation.

www.abyssinialaw.com


## 7. የዞን አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ተዋጽኦና ጥንቅር

1. የዞን አስተዳደር ምክር ቤት ከዚህ በኋላ /ም/ቤቱ/ እየተባለ የሚጠራው የሚከተሉትን የዞን አስፈፃሚ አካላት ኃላፊዎች በአባልነት አካቶ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡-

ሀ/ የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ

ለ/ የዞኑ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ

ሐ/ የግብርና መምሪያ ሃላፊ

መ/ የንግድና ትራንስፖርት መምሪያ ሃላፊ

ሠ/ የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት መምሪያ ሃላፊ

ረ/ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ ሃላፊ

ሰ/ የውሃ ሃብት ልማት መምሪያ ሃላፊ

ሸ/ የአካባቢ ጥበቃ፣የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መምሪያ ሃላፊ

ቀ/ የትምህርት መምሪያ ሃላፊ

በ/ የጤና ጥበቃ መምሪያ ሃላፊ

ተ/ የፍትህ መምሪያ ሃላፊ

ቸ/ የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች መምሪያ ሃላፊ

ኀ/ የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ

ነ/ የባህል፣ ቱሪዝምና ፖርኮች ልማት መምሪያ ኃላፊ

## 7. Composition of the Members of the Zonal Administrative Council

1. The council of zonal administration, called "***the council***" here after, is reestablished, in this regulation, by including the following heads of the zonal executive bodies:-

a) Zonal chief administrator ………… chairperson

b) Zonal deputy chief administrator …………. member

c) Head of the agricultural Department ………….. member

d) Head of the trade & transport department……………….. member

e) Head of the Industry & Urban Development department .... member

f) Head of the Finance & Economic Development department … member

g) Head of the Water Resource Development department ……. member

h) Head of the Environmental Protection, Rural Land Administration & Use department …………..….. member

i) Head of the Education department………………….. member

j) Head of the Health Department ……………..….. member

k) Head of the Justice department……………….... member

l) Head of the Administration & Security Affairs department……...….member

m) Head of the Women, Children & Youth's Affair department…. Member

n) Head of the Culture, Tourism & Parks'

www.abyssinialaw.com


ኘ/ የሲቪል ሰርቪስ ጉዳዮች ማሜሪያ ኃላፊ

አ/ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ማሜሪያ ኃላፊ

ከ/ የቴክኒክና ሙያ ማሜሪያ ኃላፊ

2. የዞን ምክትል ዋና አስተዳዳሪ በምክር ቤቱ ውሳኔ መሠረት ደርቦ የሚመራውን አስፈፃሚ መሥሪያ ቤት ሃላፊነት ጭምር እንደያዘ በምክር ቤቱ ወስጥ የሚኖረው ድምጽ አንድ ብቻ ይሆናል።

3. የዞኑ ገቢዎችና ኮሙኒኬሽን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ኃላፊዎች በምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይ እኩል ድምጽ ኖሯቸው ይሣተፋሉ።

## 8. ስለ ምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የውሣኔ አሠጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1. የዞን አስተዳደር ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባውን በአሥራ አምስት ቀን አንድ ጊዜ ያካሂዳል። ሆኖም ይህ ድንጋጌ እንደአስፈላጊነቱ የሚጠሩ አስቸኳይ ስብሰባዎችን መከናወን የሚያግድ አይሆንም።

2. ማናቸውም የምክር ቤቱ አስቸኳይ ስብሰባ በዋና አስተዳዳሪው ጥሪ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት መካከል በአንድ ሶስተኛ በሚሆኑት ጠያቂነት ሊካሄድ ይችላል።

3. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ የምክር ቤቱ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

4. ማናቸውም የምክር ቤቱ ውሣኔ የሚያልፈው

Development department…..member

o) Head of the Civil Service Affairs department ………………..member

p) Head of the Labor & Social Affairs department …………………..member

q) Head of the Technical & Vocational Education Training department …………………. member

2. The deputy chief zonal administrator shall, in addition to being the head of and directing the executive office combined in accordance with the decision of the council, have only one vote.

3. Heads of the zonal revenues and communication branch offices participate on the meeting of the council by having equal vote.

## 8. Meeting Time and Decision Making Procedure of the Council

1. The council of zonal administration shall convene its regular meeting once in fifteen days; provided, however, this provision shall not obstruct the completion of extra ordinary meetings called as deemed necessary.

2. Any extra ordinary meeting of the council may be convened by the call of the chief administrator or by the request of one-third members of the council.

3. There shall be a quorum where above half members of the council are presented at the meeting.

4. Any decision of the council shall be passed

www.abyssinialaw.com


በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት አብላጫ ድምጽ ይሆናል። ሆኖም ድምፁ ከሁለት የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ወገን የምክር ቤቱ ውሣኔ ወይም አቋም ሆኖ ያልፋል።

5. ከዚህ በላይ በዚህ አንቀጽ የሠፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን ዝርዝር የስብሰባ ጊዜና ውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት መወሰኛ መመሪያ ሊያወጣና በሥራ ላይ ሊያውል ይችላል።

## 9. ስለ ሠነዶች አያያዝና አጠባበቅ

1. የዞን አስተዳደር ምክር ቤት የሚቀርበትና የሚጋገርበት ማቸወም ጉዳይ በቃለ-ጉባኤ ይያዛል፣ በስብሰባው ላይ የተገኙ የምክር ቤት አባላትም በሰነዱ ላይ ፊርማቸውን ይኖራሉ፣

2. ማቸወም አጀንዳ ተመክሮበት የምክር ቤቱ ውሣኔ ወይም መሠረታዊ አቋም ሆኖ ለሚመለከታቸው ክፍሎች በይፋ እስከሚገለጽ ድረስ ሠነዱ በጥንቃቄ ሚዛና በምስጢር ማጠበቅ ይኖርበታል።

## ክፍል ሦስት

by a majority vote of the members of the council presented at the meeting. In case of a tie, however, the group involving the chairperson shall pass as a decision or stand of the council.

5. Without prejudice to the provisions of this article stated above, the council may issue its own detailed determination directive of meeting time and internal working procedure, and implement it.

## 9. Managing and Handling Documents

1. Any document of agenda shall, until it is deliberated and being the decision or the fundamental stand of the council and made official to the concerned bodies, be held by a minute.

2. Any issue that is deliberated and discussed by the council of zonal administration shall be held by minute. Members of the council presented at the meeting shall put their signature on the document.

www.abyssinialaw.com


## ሦስ ዋና አስተዳዳሪውና ሌሎች የዞን አስተዳደር ም/ቤት አባላት አሰያየም፣ ተጠሪነት፣ ሥልጣንና የፖለቲካ ማዕከል

## PART THREE DESIGNATION, ACCOUNTABILITY, POWER AND POLITICAL CENTER OF THE CHIEF ADMINISTRATOR AND OTHER MEMBERS OF THE COUNCIL OF ZONAL ADMINISTRATION

### 10. ስለ ዋና አስተዳዳሪው አሠያየምና ተጠሪነት

1. የዞን ዋና አስተዳዳሪ በክልሉ ርዕሰ ማስተዳድር ተመርጦ ይሾማል።
2. የዋና አስተዳዳሪው ተጠሪነት ለርዕሰ ማስተዳደሩ ይሆናል።

### 10. Designation and Accountability of the Chief Administrator

1. The zonal chief administrator shall be selected and appointed by the head of the regional government.
2. The accountability of the chief administrator is to the head of the regional government.

### 11. የዋና አስተዳዳሪው ሥልጣንና ተግባር

1. ዋና አስተዳዳሪው የዞኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ የአስተዳደር ምክር ቤቱ ሰብሳቢ ነው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ /1/ ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ደንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳዳሪው በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ልዩ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

### 11. Powers and Duties of the Chief Administrator

1. The chief administrator is the main executive body and the chairperson of the council of administration.
2. Without prejudice to the general provision stated under sub article /1/ of this article, the chief administrator shall, pursuant to this regulation, have the following special powers and duties:-

www.abyssinialaw.com


ሀ/ ርዕሰ መስተዳድሩን ወክሎ ዞኑን ያስተዳድራል፣

ለ/ በዞኑ ወስጥ የሚካሄደዉን የልማት ሥራ በበላይነት ይመራል፤

ሐ/ በዞኑ ወስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ተቋማት ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ሥራቸዉን ያስተባብራል፣ ድጋፎችን ይሰጣል፣

መ/ የአካባቢዉን ሠላምና ደህንነት ለማጠበቅ ይቻል ዘንድ በዞኑ ወስጥ ሕግና ሥርዓትን እንዲያስከብሩ የተቋቋሙትን የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

ሠ/ የዞኑን የሥራ እንቅስቃሴ እየተከታተለ ለርዕሰ መስተዳድሩ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ያቀርባል፣

ረ/ በርዕሰ መስተዳድሩና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናወናል።

## 12. ስለ ምክትል ዋና አስተዳዳሪው አሠያየምና ሥልጣን

1. የዞኑ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ በርዕሰ መስተዳድሩ ይሾማል፣

2. ምክትል ዋና አስተዳዳሪው ተጠሪነቱ ለዋና አስተዳዳሪውና ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል፣

3. ምክትል ዋና አስተዳዳሪው

ሀ/ በዋና አስተዳዳሪው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናወናል፣

ለ/ ዋና አስተዳዳሪው በማይኖርበት ወይም ሥራዉን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሰራል።

a) Administer the zone on behalf of the head of the regional government;

b) Superintend over developmental activities convened in the zone;

c) Follow-up and co-ordinate the overall activity of various branch offices and other institutions as well as render necessary support thereto;

d) Manage and supervise over the security and police forces established to maintain law and order within the zone so as to be able to protect local peace and security;

e) Submit periodic reports to the head of the government in pursuance of the activities of the zone;

f) Perform such other duties as may be assigned to him by the head and council of the regional government.

## 12. Designation and Power of the Deputy Chief Administrator

1. The zonal deputy chief administrator shall be appointed by the head of the regional government;

2. The deputy chief administrator shall be accountable to the zonal chief administrator and the head of the regional government;

3. The deputy chief administrator shall:-

a) Perform such duties as may be specifically delivered to him by the chief administrator;

b) Act on behalf of the chief administrator in his absence or under the circumstances where he is unable to perform his duties.

www.abyssinialaw.com


4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ሥር የተጠቀሱት ድንጋጌዎች የዞኑ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ ደርቦ ከሚዋው አስፈፃሚ አካል ሥልጣንና ሃላፊነት ጋር እንዳይቃረኑ ተደርጐ ይሰራባቸዋል፡፡

## 13. ስለ ሌሎች የዞን አስተዳዳር ምክር ቤት አባላት አሠያየም፣ ተጠሪነትና ሥልጣን

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 11 እና 12 ሥር ከተጠቀሱት ውጭ ያሉት ሌሎች የዞን አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በዋና አስተዳዳሪው አቅራቢነት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሾማሉ፡፡ ተጠሪነታቸውም ለዋና አስተዳዳሪውና ለሾማቸው አካል ይሆናል፡፡

2. ዋና አስተዳዳሪው የእጩ ተሿሚዎቹን ዝርዝር ለርዕሰ መስተዳድሩ ከማቅረቡ በፊት አግባብ ያላቸውን የክልል አስፈፃሚ አካላት አስተያየት በቅድሚያ ማጠየቅ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ጥያቄው የቀረበለት የክልል አስፈፃሚ አካል በአንድ ሣምንት ጊዜ ወስጥ አስተያየቱን ካልሰጠ በሹመት ሃሳቡ እንደተስማማ ይቆጠራል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ሥር የሠፈረው ድንጋጌ ቢኖርም በወል ሃላፊነታቸው ከሚጸመት ተግባርና ከሚያሳልፉት ውሣኔ ውጭ ባሉት የተናጠል ሥራዎቻቸው የዞን አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ተጠሪነት ለየሚመሯቸው አስፈፃሚ አካላት እናት መሥሪያ ቤቶች ይሆናል፡፡

4. The provisions stated under sub article /2 and 3/ of this article shall be operated with no contrast to the power and responsibility of the executive body combined and directed the zonal deputy chief administrator.

## 13. Designation, Accountability and Powers of Other Members of the Council of Zonal Administration

1. Other members of the council of zonal administration that are out of those mentioned under article 11 and 12 of this regulation, proposed by the chief administrator, shall be appointed by the head of the regional government. They are accountable to the chief administrator and to the body who appointed.

2. The chief administrator shall prior to proposing the lists of candidates to the head of the regional government, ask for recommendations from relevant regional executives; provided, however, if the regional executive body that submits the request does not give its comment within a week, it shall be taken to be agreed on the proposal.

3. Notwithstanding the provision stated under sub art. /1/ of this article hereof, members of zonal administrative council shall be, for their individual work, accountable to the office - executive organs directed by them in mother institution, except their common responsibility performance of duty and decisions rendered.

www.abyssinialaw.com


## 14. ስለ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት

1. ዋና አስተዳዳሪው በዚህ ደንብ መሠረት የተጣለበትን ሃላፊነት ለመወጣት በዞኑ የፖለቲካ ማእከል የሚቋቋም የራሱ ጽ/ቤት ይኖረዋል።
2. የዋና አስተዳዳሪው ጽ/ቤት የዞኑ አስተዳደር ምክር ቤት ጽ/ቤት ጭምር በመሆን ያገለግላል፣
3. ጽ/ቤቱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ድጋፍ ሠጭ ሠራተኞችና ኤክስፐርቶች ይኖሩታል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ሥር የሠፈሩት ድንጋጌዎች ቢኖሩም የዞኑ አስተዳደር ጽ/ቤት የብሔራዊ ክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና ክልል መስተዳድር ምክር ቤቱ ጽ/ቤት የበታች አደረጃጀት እንደመሆኑ መጠን ከዚሁ አካል ጋር በክትትል፣ በቁጥጥርና በድጋፍ አገልግሎት አሠጣጥ ላይ ያተኮረ ጥብቅ የሥራ ግንኙነት ይኖረዋል።
5. የጽ/ቤቱን ህጋዊ አቋም፣ ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቶች በሚመለከት አግባብነት ያላቸው የአዋጅ ቁጥር 65/1994 ዓ.ምና የአዋጅ ቁጥር 176/2003 ዓ.ም ድንጋጌዎች ከዚህ ደንብ ጋር ተጣጥመው ይሰራባቸዋል።

## 15. ስለ ጽ/ቤቱ ኃላፊ አሿሿምና ተጠሪነት

1. የዞን አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ የትምህርት ዝግጅትን፣ የሙያ ብቃትንና የሥነ-ምግባር ምሉዕነትን ታሣቢ በማድረግ የካቢኔ ደረጃ ተሰጥቶት በዞኑ ዋና አስተዳዳሪ የሚሾም ሲሆን ሹመቱን የዞኑ አስተዳደር ምክር ቤት ተቀብሎ እንዲያፀድቀውና የርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት እንዲያውቀው መደረግ ይኖርበታል።

## 14. The Office of Zonal Administration

1. The chief administrator shall have his own office, established by the zonal political center, in order to be able to discharge the responsibilities entrusted to him by virtue of this regulation.
2. The office of the chief administrator shall serve by being, in addition, the office of the council of zonal administration.
3. The office shall have experts and support staff necessary for the accomplishment of its task.
4. Notwithstanding the provisions stated under sub art. /1 and 2/ of this article hereof, the zonal administrative office shall, being the lower level organization of the office of the head of national regional state and council of the regional government, have a firm work relation with same body concerning on follow-up, supervision and support service provision.
5. Concerning about the legal stand, detailed duties and responsibilities of the office, the provisions of proclamation No.65/2002 and 176/2010. shall be operated in correspondence with this article.

## 15. Appointment and Accountability of the Head of the Office

1. The head of zonal administration office shall, considering educational qualification, professional efficiency, and ethical adequacy, be appointed and given a level of cabinet by the chief administrator of the zone. The appointment shall be approved

www.abyssinialaw.com



2. የጽ/ቤት ሃላፊው ተጠሪነት ለዋና አስተዳዳሪው ይሆናል።

3. የጽ/ቤቱ ኃላፊ የዞኑ አስተዳደር ምክር ቤት ፀሐፊ በመሆን ያገለግላል፣ በምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይም ያለድምጽ ይሳተፋል፣ ሃሳቦችና አስተያየቶች ይሰጣል።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 16. ስለ ተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማኖራቸው ህጎች

1. የሚከተሉት ህጎች በዚህ ደንብ ተሽረዋል፡-

   ሀ/ የዞን አስተዳደር ጽ/ቤቶች ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ ክልል ማስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 1/1994 ዓ.ም፤

   ለ/ የዞን አስተዳደር ካቢኔዎች ሚደራጀና የወል ተግባርና ሃላፊነት መወሰኛ መመሪያ ቁጥር 1/1994 ዓ.ም፡

2. ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ ወስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡

### 17. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

ቀደም ሲል በክልል ማስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር

by the council of zonal administration and recognized by the office of the head of the government.

2. The accountability of the head of the office of zonal administration is to the chief administrator.

3. The head of the office shall serve as the secretary of the council of zonal administration, participate, and give comments at the council meetings without vote.

## PART FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 16. Repealed and Inapplicable Laws

1. The following laws are repealed hereby this regulation:-

   a) The Establishment and Determination of Powers and Duties Council of Regional Government Regulation No 1/2001.

   b) The Zonal Administration Cabinets Organization and Determination of Common Duties and Responsibilities Directive No 1/2001

2. Any other regulation, directive, or customary Practice inconsistent with this regulation shall not apply to matters provided for in this regulation.

### 17. Transfer of Rights and Duties

The rights and duties that were given to

www.abyssinialaw.com


1/1994 ዓ.ም ተቋቁመው ለነበሩት የዞን አስተዳደር ጽ/ቤቶች የተሰጡት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ መሠረት እንደገና ወደ ተቋቋሙት የዞን አስተዳደሮች ተላልፈዋል።

## 18. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ርዕሰ ማስተዳደሩ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣና በሥራ ላይ ሊያውል ይችላል።

## 19. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ ማግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

ህዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልል

ማስተዳድር ም/ቤት

the zonal administrative offices established before by the Council of Regional Government Regulation No 1/2001 are hereby transferred to the zonal administrations re-established under this regulation.

## 18. Power to Issue Directive

The head of the government may issue and enforce directives necessary for the implementation of this regulation.

## 19. Effective Date

This regulation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre-Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar

This 12th day of November, 2010

Council of the Amharic National

Regional State